‹‹ከትንሳኤ ቀን ችግሮች አላህ እንዲገላግለው ያስደሰተው ሰው ለችግርተኛ ፋታ ይስጥ ወይም ከርሱ ያቅልልለት።

ከአቡ ቀታዳህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: «አቡ ቀታዳህ አንድ ተበዳሪውን
ሲፈልገው ከርሱ ተሸሸገ። ከዚያም አገኘው። ተበዳሪውም "እኔ ችግርተኛ ነኝ።" አለው። እርሱም "ወላሂ በል!" አለው። ተበዳሪውም "ወሏሂ!" አለ። አቡቀታዳም እንዲህ አለ: "እኔ የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ:‐ ‹‹ከትንሳኤ ቀን ችግሮች አላህ እንዲገላግለው ያስደሰተው ሰው ለችግርተኛ ፋታ ይስጥ ወይም
ከርሱ ያቅልልለት።»
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

አቡቀታዳህ አልአንሷሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ከርሱ ይደበቅ የነበረን ተበዳሪን ይፈልግ ነበርና አገኘው። ተበዳሪውም እንዲህ አለው "እኔ ችግርተኛ ነኝ። እዳህን የምከፍልበት ገንዘብም የለኝም።" አቡቀታዳህም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ገንዘብ እንደሌለው ምሎ እንዲነግረው ጠየቀው። በሚናገረው ነገር እውነቱን እንደሆነም በአላህ ምሎ ነገረው። አቡ ቀታዳህም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ እነደደሰማ ተናገረ: አላህ ከትንሳኤ ቀን ችግሮችና ጭንቆች እንዲያድነው ያስደሰተው ሰው ከችግርተኛ ያቅልል። ይህም መክፈያ ጊዜውን በማዘግየትና በማርዘም ወይም የተወሰነውን እዳ ወይም ሁሉንም ይቅር በማለት ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/4195